# ኢትዮጵያ

## እድገት የለም - ጥረቶች ተደርገዋል ነገር ግን በግዳጅ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን በሚመለከት ቸልተኞች ሆነው ተገኝተዋል።

በ2024 (2016/2017) ኢትዮጵያ ላይ የተካሄደው ግምገማ ምንም እድገት እንዳልተመዘገበ ያሳያል። ኢትዮጵያ ውስጥ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን ለማስቀረት ጅምሮች ቢኖሩም ምንም አይነት እድገት አላስመዘገቡም፥ ምክንያቱም ኢትዮጵያ በግዴታ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ላይ ተባባሪ መሆኗን አሳይታለች። ሪፖርቱ በሚሸፍነው ግዜ ውስጥ በመንግስት እና ከመንግስት ጋር ተባባሪ የሆኑ የጸጥታ ሃይሎች በግዳጅ ለውትድርና መመልመልን ጨምሮ በልጆች ወታደሮች ጉዳይ ላይ ኦፊሴላዊ ቸልተኝነት መኖሩን የሚያመለክቱ ሪፖርቶች ወጥተዋል። ተሰንደው ያሉ መረጃዎች ባለመኖራቸው ምክንያት የጸጥታ ሃይሎች ሕጻናትን እያወቁ መመልመላቸው ግልፅ አልነበረም። በኦሮሚያ ክልል ለወታደራዊ ስልጠና በታጣቂ ሃይሎች በዘፈቀደ ተይዘው የታሰሩ ሕጻናት ከ14 የማያንሱ ሲሆኑ፣ አንደኛው ህጻን እድሜው 11 ዓመት ነው ተብሎ ሪፖርት ተደርጓል። አንዳንድ ሁኔታዎች እንደሚጠቁሙት ልጆቻቸውን ወደ ወታደራዊ ማሰልጠኛ እንልክባችኋለን እያሉ ቤተሰቦችን በማስፈራራት ልጆቻቸውን ለማስለቀቅ ቤተሰቦች ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ እንዲከፍሉ ተጠይቀዋል። ከዚህ በተረፈ፥ መንግስት ከተባበሩት መንግስታት የሕጻናት መርጃ ድርጅት ጋር በመሆን የተጠናከረ የሕጻናት ጥበቃ ጉዳይ አስተዳደር መረጃ ስርዓት በመዘርጋት የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን ለማስወገድ እና ለመከላከል ጥረት አድርጓል። ይህ አዲስ የመረጃ ስርዓት የተማከለ የመረጃ ማከማቻ እጥረት ችግርን ለመፍታት ይሰራል፤ ይህም ከክልሎች የተገኙ መረጃዎችን፣ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን የሚመለከቱ መረጃዎችን እና ሚስጥራዊነት ያለው የግል መለያ መረጃን የሚያካትት ነው። በተጨማሪም፥ መንግሥት በኤፕሪል 4, 2024 (መጋቢት 26 ቀን 2016 ዓም) የግል መረጃ ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 1321/2024 አጽድቋል፤ ይህም አዋጅ ከ16 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ እንደሆነ ይደነግጋል፤ እና ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ የግል መረጃን ለማግኘት የወላጅ ወይም የአሳዳጊ ፈቃድ መኖር እንዳለበት የሚደነግግ ሲሆን፤ የሕጻናትን መብት ማስቀደም እንዳለበት ይደነግጋል። ይሁን እንጂ እነዚህ ጥረቶች ቢኖሩም የኢትዮጵያ ሕጎች ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን አያሟሉም፤ ምክንያቱም ልጅን ለወሲብ ንግድ መጠቀምን እንደ ወንጀል ስለማይቆጥሩ እና እድሜያቸው 15 እና 16 የሆኑ ሕጻናት በአደገኛ ስራ እንዲሰማሩ ስለሚያስችል ነው። በተጨማሪም፥ አደገኛ የሥራ መከላከያዎች ባሕላዊ ሽመናን አይጨምሩም፤ በዚህ የሥራ መስክ ውስጥ ሕጻናት አደገኛ ማሽኖችን፤ መሳሪያዎችን እና ቁሶችን እንደሚጠቀሙ የሚያሳይ መረጃ አለ። በተጨማሪ፥ የኢትዮጵያ ሕግ ነፃ መሰረታዊ ትምህርትን ወይም ትምህርት በስንት ዓመት መጨረስ እንዳለበት ስለማያካትት ሕፃናት ለከፋ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ እንዲጋለጡ አድርጓል። እንዲሁም፥ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን ለማሰቀረት ማህበራዊ ፕሮግራሞች፥ ግብርና እና የቤት ውስጥ ሥራን ጨምሮ ከፍተኛ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ያለባቸው ዘርፎች ላይ በበቂ ሁኔታ አላነጣጠሩም።

## የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን ለማስወገድ የተጠቆሙ የመንግስት እርምጃዎች

ከዚህ በታች የተጠቆሙ USDOL የለያቸው የመንግስት እርምጃዎች ኢትዮጵያ የከፋ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን ለማስወገድ የገባችውን ዓለም ዓቀፍ ቃል ኪዳን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ክፍተቶችን የሚያጠብ ይሆናል።

| መስክ | መወሰድ ያለበት እርምጃ ጥቆማ |
|---|---|
| **የህግ ማዕቀፍ** | ሕጻናትን ለወሲባዊ ንግድ ብዝበዛ መጠቀምን በወንጀል መከልከል። |
| | በILO ስምምነት 138 መሠረት ከሙያ ስልጠና በኋላ ሕጻናት ወደ አደገኛ ሥራ ሊገቡ የሚችሉበትን አነስተኛ ዕድሜ ወደ 16 ዓመት በማሳደግ፥ የILO ኮንቬንሽን 138ን በማክበር ባህላዊ ሽመናን ጨምሮ አደገኛ ማሽኖችን፣ መሳሪያዎችን እና ቁሶችን ጨምሮ ሕጻናት ሁሉንም ዓይነት አደገኛ ስራዎች ላይ እንዳይሰማሩ መከልከል። |
| | መንግስታዊ ባልሆኑ የታጠቁ ቡድኖች ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናትን ለውትድርና መመልመልን ሕጉ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ ድርጊቱን እንዲከለክል ማድረጉን ማረጋገጥ። |
| | ነፃ መሰረታዊ ትምህርት የሚሰጡ ሕጎች በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሁሉንም ሕጻናት፥ ዜጋ ያልሆኑትንም ጭምር የሚያጠቃልሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ። |
| | በሕግ የግዴታ የትምህርት እድሜ እስከ 15 ዓመት የቅጥር እድሜ ጋር እንዲስማማ አድርጎ መመስረት። |
| **ማስከበር** | ለውትድርና ስልጠና እና ቅጥር ዓላማ ሕጻናትን በግዳጅ ማሰርን እና መመልመል ማስቆም፤ ሕጻናትን ወደ ውትድርና በመመልመል ላይ የተሳተፉትን የወታደራዊ ባለስልጣናትን ጉዳይ መመርመር። |
| | ከታጣቂ ቡድኖች ጋር ግንኙነት ያላቸው ሕጻናት ወደ ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪዎች መላካቸውን ማረጋገጥ እና ሕጻናትን እንደ አዋቂ ሰው አድርጎ የማሰር ልምድን ማቆም። |

| መስክ | መወሰድ ያለበት እርምጃ ጥቆማ |
|---|---|
| | የሠራተኛ ተቆጣጣሪዎች በቢሮዎች፣ በመጓጓዣ፣ በነዳጅ፣ በግላዊ መከላከያ ልብሶች እና አደገኛ ሁኔታዎችን ለመገምገም የሚረዱ መሳሪያዎችን ጨምሮ በሁሉም ዘርፎች ላይ ቁጥጥር ለማድረግ ይችሉ ዘንድ በቂ ሀብቶችን ማቅረብ፣ በግምት ወደ 38.5 ሚሊዮን የሚጠጉ የሰራተኞች ላይ በቂ ሽፋን ለማድረግ የሰራተኛ ተቆጣጣሪዎችን ቁጥር ከ500 እስከ 600 የሚሆኑትን ወደ 964 ማሳደግ፤ እና በዓለም አቀፍ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ደረጃዎች ላይ ተጨማሪ ስልጠና በመስጠት የሰራተኛ ተቆጣጣሪዎችን አቅም በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ፤ እና በሀገር ዓቀፍ እና በክልል አስከባሪ ኤጀንሲዎች መካከል ያለውን ቅንጅት ማጠናከር። |
| | የተቆጣጣሪዎች ብዛት፣ የተቆጣጣሪ ድርጅት የገንዘብ ድጋፍ፥ የታለሙ መደበኛ ፍተሻዎች እንዳሉ እና በሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ላይ የሚጣሉ እና የተሰበሰቡ ቅጣቶችን ጨምሮ የሰራተኛ ሕግ አስከባሪ መረጃዎችን በጽሁፍ ማውጣት። |
| | ለወንጀል ሕግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች የገንዘብ ድጋፍ መጨመር። |
| | በአገር ውስጥም ሆነ በድንበር ዘለል ደረጃ የሕጻናት ዝውውር ጉዳዮችን መመርመር፣ ወንጀለኞችን ሁሉ በፍትህ ስርዓት ለፍርድ ማቅረብ፣ የሕጻናትን ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀለኛነት እና የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን እንዲሁም የወሲባዊ ንግድ ብዝበዛን ጨምሮ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት። |
| **ማስተባበር** | በኮሚቴ መካከል ያለውን ግንኙነት፣ ቅንጅት እና ትብብርን ለማሳደግ በብሔራዊ የአስተባባሪ ኮሚቴ ውስጥ ተሳታፊዎች የግለሰብ አደራዎችን ግልጽ ማድረግ እና በልጆች ጥበቃ ላይ የስልጠና እድሎችን ማሳደግ። |
| | ከአስከፊው የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ጋር የተያያዙ ተግባራትን የሚፈጽሙ አካላት በብቃት እንዲያቀናጁ ለማድረግ ለአስተባባሪ አካላት በቂ ገንዘብ መመደብ። |
| **የመንግስት ፖሊሲዎች** | በትምሕርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ውስጥ በብሔራዊ የቴክኒክ እና ሙያ ትምሕርት እና ሥልጠና ስትራቴጂ እና በብሄራዊ የወጣቶች መመሪያ የሕጻናት የጉልበት ብዝበዛን የማስወገድ እና የመከላከል ስልቶችን ማቀናጀት። |
| | ከሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ጋር የተያያዙ ቁልፍ ፖሊሲዎችን በየዓመቱ ተግባራዊ ለማድረግ የተከናወኑ ተግባራትን፣ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን ለማስወገድ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብርን፣ የአምስት ዓመት የስደተኞች አስተዳደር ስትራቴጂክ እቅድ እና የትምህርት ስልጠና ፖሊሲን ጨምሮ ማተም። |
| **ማህበራዊ ፕሮግራሞች** | የትምህርት ቤት ሕንፃዎችን መጠገን እና እንደገና እንዲከፈቱ ማድረግ፣ ሁሉንም የታጠቁ ቡድኖችን ከትምህርት ተቋማት ማስወገድ እና ተማሪዎች እና መምህራን ለትምህርት ዓላማ በሰላም እንዲሰባሰቡ አስፈላጊ ጥበቃ ማድረግ። |
| | የዩኒፎርም፣ የአቅርቦቶች እና የምግብ ክፍያዎችን በማስወገድ ለሁሉም ልጆች የትምህርት ተደራሽነትን ማሳደግ፤ ትምህርት ቤት እና ወደ ትምህርት ቤት በሚመላለሱበት መንገድ ላይ የተማሪን ደህንነት ማረጋገጥ፤ በቂ ቁጥር ያላቸውን አስተማሪዎች እና የንፅህና አጠባበቅ ተቋማትን በተለይም ለሴቶች ልጆች ማረጋገጥ፤ እንዲሁም የአካል ቅጣትን መጠቀምን ማስቆም። በመጨረሻም፥ በተለይም የአካባቢውን ቋንቋ መናገር ለማይችሉ እና በሃገር ውስጥ ከመኖሪያ ቤታቸው ለተፈናቀሉ ሕጻናት የቋንቋ ፍላጎትቻቸውን ማስተናገድ። |
| | የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ትምህርታቸውን መከታተል እንዲችሉ ለመምህራን ስልጠና መስጠት እና ትምህርት ቤቶች ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ። |
| | የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን ለመከላከል እና ለማጥፋት አስፈላጊ የሆኑ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ማለትም የመልሶ ማቋቋም እና የመልሶ ማዋሃድ ማዕከላትን በመላ ሀገሪቱ መኖራቸውን ማረጋገጥ እና የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን በግብርና፣ በመንገድ ላይ እና በቤት ውስጥ ስራ ጨምሮ በሁሉም ዘርፎች ለመፍታት የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት ወይም ማስፋፋት። |